መልእክት አምስት

## እግዚአብሔር እንደ ሉዓላዊ ሸክላ ሠሪአችን
## እርሱን ለመያዝ እኛን ማድጋዎቹ፣ መያዣ ዕቃዎቹ ማድረጉ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኤር. 18፡1-10፤ ኢሳ. 64፡8፤ ሮሜ 9፡15-16፣ 19-23፤ ሐዋ. 9፡15፤ 2 ቆሮ. 4፡6-7

**I. እግዚአብሔር እንደ ሉአላዊው ሸክላ ሠሪአችን በእኛ ላይ እንደ ሸክላ ዕቃዎቹ ሙሉ መብት አለው፤ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ራእይ ማየታችን እጅግ አስፈላጊ ነው—ኤር. 18፡1-10፤ ኢሳ. 64፡8፤ ዳን. 4፡3፤ 34-35፤ ሮሜ 9፡19-23፦**

ሀ. ሉዓላዊነት የእግዚአብሔርን ያልተገደበ ሥልጣን፣ ኃይል እና ስፍራ ያመለክታል—ራእ. 4፡11፤ 5፡13፦

1. እንደ ሉዓላዊው ማንነት፣ እግዚአብሔር ከሁሉ ነገር በላይ፣ ከሁሉ ነገር በስተጀርባ እና በሁሉ ነገር ውስጥ ነው—1ነገ. 22፡19።
2. እግዚአብሔር በልቡ መሻት መሠረት እና በዘላለማዊው ኢኮኖሚው መሠረት የሚፈልገውን ለማከናወን ሙሉ አቅም አለው—ዳን. 4፡34-35፤ ኤፌ. 1፡4-5፣ 9-11።

ለ. ሮሜ 9፡19-23 የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ያመለክታል፦

1. "...ፈቃዱንስ የሚቃወም ማን ነው?... ነገር ግን፣ አንተ ሰው ሆይ፣ ለእግዚአብሔር የምትመልስ ማን ነህ? ሥራ ሠሪውን፦ ስለ ምን እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ይለዋልን?"—ቁ. 19-20፦
   ሀ. ማን እንደሆንን መገንዘብ ያስፈልገናል፤ እኛ የእግዚአብሔር ፍጥረታት ነን፣ እርሱም ፈጣሪያችን ነው—ኢሳ. 42፡5።
   ለ. እንደ ፍጥረታቱ፣ ዓላማውን መቃወም ወይም ለእርሱ፣ ለፈጣሪው መመለስ የለብንም—ሮሜ 9፡20።
2. "ወይም ሸክላ ሠሪ ከአንዱ ጭቃ ክፍል አንዱን ዕቃ ለክብር አንዱንም ለውርደት ሊሠራ በጭቃ ላይ ሥልጣን የለውምን?"—ቁ. 21፦
   ሀ. እግዚአብሔር ሸክላ ሠሪአችን ነው፣ እኛም በእጁ ውስጥ ያለን ሸክላ ነን፤ ሸክላ ሠሪአችን እግዚአብሔር ሉዓላዊ ነው—ኤር. 18፡1-6፤ ኢሳ. 64፡8።
   ለ. እንደ ሸክላ ሠሪአችን እግዚአብሔር በእኛ ላይ ሙሉ መብት አለው፤ እኛን በተመለከተ፣ ያሻውን ሁሉ ለማድረግ መብት አለው፤ እግዚአብሔር ከፈቀደ አንዱን ዕቃ ለክብር ሌላኛውንም ዕቃ ለውርደት ማድረግ ይችላል—ኤር. 18፡6፤ ኢሳ. 29፡16፤ 64፡8፤ ሮሜ 9፡21።

ሐ. የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት የምርጫው መሠረት ነው፤ የእርሱ ምርጫ በሉዓላዊነቱ ላይ ይመረኮዛል—ቁ. 11፣ 18፤ 11፡5፣ 28።

**II. እግዚአብሔር እንደ ሸክላ ሠሪአችን በቀደመ ውሳኔው መሠረት እርሱን ራሱን ለመያዝ፣ ማድጋዎቹ፣ መያዣ ዕቃዎቹ እንድንሆን በሉዓላዊነቱ ፈጠረን—2 ቆሮ. 4፡6-7፤ ኤፌ. 4፡6፤ 3፡19፤ ፊልጵ. 2፡13፤ ዕብ. 13፡20-21፤ 1 ጢሞ. 3፡16፤ 2 ጢሞ. 2፡20-21፤ ኤፌ. 1፡5፣ 11፦**

ሀ. እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረበት ዓላማ ለመገለጡ እንዲሆን የእግዚአብሔር ታላቅ፣ ብዙዎች የተካተቱበት ማድጋ፣ ለክርስቶስ አካል መገንባት እንደ ሕይወት ክርስቶስን ለመያዝና በክርስቶስ ለመሞላት፣ ሰውን ከሸክላ የተሠራ የእርሱ መያዣ ለማድረግ ነበር—ዘፍ. 2፡7፤ ሐዋ. 9፡15፤ ሮሜ 9፡21፤ 23፤ 2 ቆሮ. 4፡7።

ለ. የመላው መጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊው ትምህርት በቀላሉ ይህ ነው፦ እግዚአብሔር ይዘቱ ነው፣ እኛ ደግሞ ይዘቱን ለመቀበል የተሠራን መያዣዎች ነን፤ ለክብር የሚሆኑ ዕቃዎች፣ የተቀደሱ፣ ለጌታ የሚጠቅሙ፣ ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጁ መሆን እንችል ዘንድ እግዚአብሔርን መያዝና በእግዚአብሔር መሞላት አለብን—2 ጢሞ. 2፡20-21።

ሐ. እግዚአብሔርን ካልያዝንና እንደ ይዘታችን እግዚአብሔርን ካላወቅን፣ ትርጉም-አልባ እርስ በእርሳቸው የሚጣረሱ ነን—መክ. 1፡2-3፣ 14።

መ. የጳውሎስ አሥራ አራቱ መልእክቶች ሁሉም በሁለት ቃላት ሊጠቃለሉ ይችላሉ—*ክፍት ዕቃ*፦

1. እግዚአብሔር ራሱን ወደ እኛ ውስጥ ማደል የሚችልበት ልክ የሚወሰነው በመከፈታችን ልክ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱን እንድንወደውና ራሳችንን ለእርሱ ክፍት አድርገን እንድንቆይ ብቻ ይፈልጋል—2 ነገ. 4፡1-7፤ ማቴ. 5፡3፤ ዮሐ. 1፡16፤ ኢሳ. 57፡15፤ 66፡1-2።
2. ዝቅጠት በራስ ከመርካት ይጀምራል፤ እድገት ከረሃብና ጥማት ይጀምራል—ዘዳ. 4፡25፤ ሉቃ. 1፡53፤ ፊልጵ. 1፡25፤ ራእ. 3፡16-18።

**III. በሉዓላዊነቱ እግዚአብሔር እንደ ሸክላ ሠሪአችን የመረጣቸውንና የጠራቸውን ለምሲጋናና ለክብር የሆኑ የምሕረት ዕቃዎች እንዲሆኑ ለማድረግ ሥልጣን አለው—ሮሜ 9፡11፣ 18፣ 21-24፦**

ሀ. በሉዓላዊ ምሕረቱ መሠረት በእግዚአብሔር ተመርጠናል፤ ከጎስቋላ ስፍራችን ለጸጋውና ለፍቅሩ ምቹ ወደሆነ ሁኔታ ለማዳን የእግዚአብሔር ምሕረት ከእግዚአብሔር ባሕሪያት መካከል እጅግ ሩቅ ደረስ የሆነ ነው—ኤፌ. 2፡1-4፤ ዕብ. 4፡16፤ ማቴ. 5፡7፤ 7፡1፤ 9፡13፦

1. በፍጥረታዊ ሁኔታችን መሠረት፣ ከእግዚአብሔር የተለየን፣ ጸጋው ፈጽሞ የማይገባን ነበርን፤ ምሕረቱን ለመቀበል ብቻ ብቁ ነበርን—ኤፌ. 2፡4።
2. የሰው አለመታዘዝ ለእግዚአብሔር ምሕረት እድልን ይሰጠዋል፣ እንዲሁም የእግዚአብሔር ምሕረት ሰውን ወደ መዳን ያመጣዋል—ሮሜ 11፡32።
3. እንደ የምሕረት አምላክ ክርስቶስን ለመያዝ የምሕረት ዕቃዎች ለመሆን ተፈጥረናል—9፡11-13፣ 16፣ 20-21፣ 23፤ ሰቆ. 3፡21-24፤ ሉቃ. 1፡78-79።
4. ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ለወንጌል ምላሽ ስንሰጥ ሌሎች ምላሽ አልሰጡም፣ ክርስቶስ ሕይወት ነው የሚል ቃል ስንቀበል ሌሎች አንቀበልም አሉ፣ የጌታን ምለሳ መንገድ ስንመርጥ ሌሎች ይህን መንገድ ከመከተል ወደኋላ አሉ—ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ #296 ቁጥር 3።

ለ. "የምምረውን ሁሉ እምረዋለሁ...እንግዲህ ምሕረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም፥ ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው እንጂ"—ሮሜ 9፡15-16፦

1. የእኛ ጽንሰ-አሳብ የወደደ ለማግኘት የወደደውን ያገኛል እንዲሁም የሮጠ የሮጠለትን ያገኛል የሚል ነው—ቁ. 16፦
   ሀ. ጉዳዩ እንዲህ ቢሆን ኖሮ፣ የእግዚአብሔር ምርጫ በእኛ ጥረትና ድካም መሠረት ይሆን ነበር።
   ለ. በተቃራኒው የእግዚአብሔር ምርጫ ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር ምሕረቱን በእኛ ላይ ስላደረገ መውደድ ወይም መሮጥ አያስፈልገንም።
   ሐ. የእግዚአብሔርን ምሕረት ካወቅን በጥረታችን አንታመንም በውድቀቶቻችንም ተስፋ አንቆርጥም፤ ለተጎሳቆለው ሁኔታችን ተስፋው የእግዚአብሔር ምሕረት ነው—ኤፌ. 2፡4።
2. በአዲስ ኪዳን ኢኮኖሚው እግዚአብሔርን የምናገለግል ከሆነ፣ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምሕረት ጉዳይ መሆኑን ማወቅ ያስፈልገናል—ሮሜ 9፡15-16፤ ዕብ. 4፡16፦
   ሀ. የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ብናውቅ፣ በእርሱ ሉዓላዊ ምሕረት ሥር መሆናችንን በመገንዘብ ስለ ምሕረቱ እናመሰግነዋለን—ሮሜ 9፡15።
   ለ. *ሉዓላዊ ምሕረት* የሚለው አገላለጽ የእግዚአብሔር ምሕረት ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ጉዳይ ነው ማለት ነው፤ የምሕረት ዕቃ መሆን የእኛ ምርጫ ውጤት አይደለም፤ የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ነው—ቁ. 18።
   ሐ. ለእኛ ያለውን የእግዚአብሔርን ምሕረት ለማብራራት ማለት የምንችለው ብቸኛው ነገር በሉዓላዊነቱ ሊምረን መምረጡን ነው—ቁ. 15-16፣ 23።
3. በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምሕረት ልቦቻችን ወደ እርሱ አዘንብለዋል፤ ካደረገልን ምሕረት የተነሣ፣ ዕለት ዕለት እርሱን እንሻዋለን—ኤር. 29፡12-13፤ ዘዳ. 4፡29፤ ኢሳ. 55፡6፤ መዝ. 27፡8፤ 105፡4፤ 119፡2፤ ዕብ. 11፡6።
4. ከእኛ ጋር የተገናኘው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር ምሕረት ጉዳይ እንደ ሆነ አብልጠን ባየን ቁጥር፣ የበለጠ በጌታ ፊት ያለንን ኃላፊነታችንን እንሸከማለን፤ ሆኖም ግን፣ ኃላፊነትን ለመሸከም ፈቃደኝነታችን እንኳ የእግዚአብሔር ምሕረት ነው።
5. ምለሳውን በተመለከተ፣ እግዚአብሔር የሚምረውን ይምረዋል።

ሐ. ሮሜ 9 ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ምሕረት ላይ የመደገፉን መርህ ይገልጣል—ቁ. 15-16፦

1. በእስራኤላውያን ላይ የደረሰው ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር ምሕረት መሆኑን በማሳየት፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መርህ በእስራኤላውያን ላይ ይተገብረዋል—ቁ. 16፣ 23።
2. የእግዚአብሔርን ምሕረት የምናይበትና ተጨባጭ በሆነ መንገድ ምሕረቱን የምናገኝበት ቢያንስ አንድ ጊዜ መኖር አለበት—ኤፌ. 2፡4፤ ማቴ. 9፡13፦
   ሀ. ይህን ጉዳይ በተመለከተ፣ ዓይኖቻችን ቢያንስ አንዴ መከፈት ያስፈልጋቸዋል፤ ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ምሕረት ላይ መደገፉን የምናይበት ቢያንስ አንድ ጊዜ መኖር አለበት።

ለ. ይህን ሁሉ በአንዴ እንይ ወይ በሂደት እንገንዘበው፣ ይህን ጉዳይ በነካንበት ጊዜ፣ ስሜትን ሳይሆን ሐቅን እንነካለን፤ ይህም ሐቅ ሁሉ ነገር በእግዚአብሔር ምሕረት ላይ መደገፉ ነው።

መ. "እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ"—ዕብ. 4፡16፣ ተዛ. ቁ. 15፤ ሉቃ. 15፡20-24።

ሠ. በሉዓላዊነቱ እግዚአብሔር አብ ማረን፤ ስለዚህ ስለ ሉዓላዊ ምሕረቱ እርሱን ማወደስና ማምለክ አለብን፡-

1. "አባት ምሕረትህን እንደሰታለን፣/ ሁሌም ትኩስ ሁሌም አዲስ፤ / በየማለዳው በእኛ ላይ የፈሰሰው፣ / እንደ ጠል ያድሳል። / እንዴት አጣጣምነው! እንዴት አጣጣምነው! / የሚገባህን ምስጋና እየሰጠን"—ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ #26፣ ቁጥር 5።
2. "አባት ምሕረትህን ከፍቅርህና ጸጋህ ጋር / አገኘነው፤ / በምሕረትህም፣ ከአንተ ጋር ፊት ለፊት፣/ ለዘላለም እንቆያለን፤ / ስለምሕረትህም እናመልክሀለን / በቀኖቻችን ሁሉና ለዘላለም"—ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ #25፣ ቁጥር 3።

ረ. እግዚአብሔርንና ሰውን እናከብር ዘንድ (መሣ. 9፡9) እንደ ክብር አምላክ ክርስቶስን ለመያዝ ለክብር የሆኑ የምሕረት ዕቃዎች ለመሆን ተፈጥረናል (2 ጢሞ. 2፡20-21፤ ሮሜ 9፡21)፡-

1. የክብር ዕቃ መሆን የምርጫችን ውጤት አይደለም፤ ከእግዚአብሔር ሉዓላዊነት የሚመነጭ ነው—ሮሜ 9፡21።
2. በዳግም ውልደት አማኞች መዝገባቸው ክርስቶስ የሆነ የክብር ዕቃ ናቸው—2 ቆሮ. 4፡6-7።
3. ለውርደት ከሆኑ ዕቃዎች ራሳቸውን በማንጻት አማኞች ለክብር የሆኑ ዕቃዎች ናቸው—2 ጢሞ. 2፡20-21።
4. ለክብር የሆኑት ዕቃዎች በመንፈስ በመኖርና በመመላለስ እግዚአብሔርን የሚያከብሩ (ገላ. 5፡16፣ 25) እና ለሰዎችን መንፈስን በማገልገል ሰዎችን የሚያከብሩ ናቸው (2ቆሮ. 3፡6፣ 8)።

ሰ. እንደ የክብር አምላክ ክርስቶስን ለመያዝ ለክብር የሆኑ የምሕረት ዕቃዎች ለመሆን ተፈጥረናል፡-

1. ክብር እግዚአብሔር ራሱ ሲገለጥና ሲታይ ነው—ኤር. 2፡11፤ ሐዋ. 7፡2፤ ኤፌ. 1፡17፤ 1 ቆሮ. 2፡8፤ 1 ጴጥ. 4፡14፤ ቆላ. 2፡9፤ መዝ. 24፡7-10።
2. ጌታ ለአብ "እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ" (ዮሐ. 17፡4) ማለት ችሏል፤ ይህም ማለት ጌታ በምድር ላይ ሲኖር ሳለ፣ አብን አሳይቷል ገልጧልም።
3. የክርስቶስ የመለኮቱ ክብር መለቀቅ (ሉቃ. 12፡49-50) በሞቱ በኩል በትንሣኤው (ሐዋ. 3፡13) በመለኮታዊው ክብር በአብ መክበሩ ነበር (ዮሐ. 12፡23-24)፤ በክርስቶስ መክበር፣ እርሱ እንደ ኋለኛው አዳም ለመለኮታዊ እደላው ሕይወትን-የሚሰጥ መንፈስ ሆነ (ዮሐ. 7፡39፤ ሉቃ. 24፡26፣ 46፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ 2 ቆሮ. 3፡6)።
4. ለምስጋናና ክብር እንደሆኑ የምሕረት ዕቃዎች፣ የእግዚአብሔር ሙሉ ማዳን የመጨረሻው ደረጃ በሆነው በመክበር— ለክብር በእግዚአብሔር ተዘጋጅተናል—ሮሜ 8፡21፣ 23፣ 29-30፤ ፊልጵ. 3፡21።
5. በሉዓላዊ ሥልጣኑ መሠረት፣ እግዚአብሔር ለክብሩ ፈጠረን፣ ቀረጸን፣ እንዲሁም ሠራን—ኢሳ. 43፡7፤ ሮሜ 9፡23፡-
   ሀ. ለክቡር መገለጡና መታየቱ መያዣ ዕቃዎቹ ለመሆን በሉዓላዊነቱ አስቀድሞን ተወሰንን።
   ለ. ይህ ለእግዚአብሔር ያለን ጠቃሚነት ከፍተኛው ደረጃ ነው—በሉዓላዊነቱ መሠረት የሆነው የእግዚአብሔር ምርጫ ግብ—ቁ. 11፣ 18።
   ሐ. የእግዚአብሔር መክበር የአገልግሎታችን ዓላማ ነው—7፡6፤ 11፡36።
   መ. ለእግዚአብሔር ልንሰጠው የምንችለው ከፍ ያለው አገልግሎት ለክብሩ እርሱን መግለጥ ነው—1 ቆሮ. 6፡20፤ 10፡31፤ ሮሜ 6፡4።
   ሠ. የእግዚአብሔር ክብር ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሠርቷል፣ እርሱም በቤተ ክርስቲያን ተገልጧል፤ ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ክብሩ ለእግዚአብሔር ነው፤ ማለትም እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ከብሯል—ኤፌ. 3፡16፣ 20-21።
6. ክርስቶስ እንደ የክብር አምላክ በውስጣችን በሸክላ ዕቃዎች በማደሩ ይህ መዝገብ አለን (2 ቆሮ. 4፡7)፤ በእኛ ያደረው "ይህ መዝገብ" (ቁ. 7) "የኢየሱስ ክርስቶስ ፊት" (ቁ. 6)፣ የክርስቶስ መገኘት፣ "የክርስቶስ ማንነት" (2፡10) ነው።
7. ልባችንን ወደ ጌታ ስናዞር፣ በመንፈሳችን ውስጥ እንዳለው የክርስቶስ መገኘት ጌታ መንፈስን ትኩር ብለን እየተመለከትን ነው፣ እንዲሁም እኛ "መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር [እየተለወጥን ነው]"—3፡16-18፤ ተዛ. 2 ጢሞ. 4፡22።

8. የጌታን ክብር ትኩር ብሎ መመልከት እኛ ራሳችን ጌታን ማየታችን ነው፤ የጌታን ክብር ማብለጭለጭ ሌሎች በእኛ በኩል እርሱን እንዲያዩት ማስቻል ነው—ኢሳ. 60፡1፣ 5።

*© 2020 Living Stream Ministry*